# ነገ እምናየው ነው

አልታይሽ አላት ፣ ስራዋ ለራሷ
ፍየል ከመድረሷ ፣ ቅጠል መበጠሷ
አምና በወያኔ ፣ ዘንድሮ በኦነግ
ሱሴና ድምሮሽ ፣ ጀመሩ መውረግረግ
መገን ያራዳ ልጅ ፣ አዲሳቤ ፣ ንቃ
አብይ ሆነ ለማ ፣ አልበጁህም ይብቃ
ተደራጅተህ ታጠቅ ፣ እንዳትዘናጋ
ደም የጠማው መጥቷል ፣ ካንተ ጋር ሊዋጋ ።

እኛው ያመጣነው ፣ ወትውተን ጎትተን
ያለልኩ ቀደን ፣ ያለልኩ ሰፍተን
ያነገስነው ንጉስ ፣ ቤተመንግስት ከፍተን
እንዲህ ከመቅፀፊት ፣ ዛሬ ላይ ተረስተን
በደልና ግፉን ፣ በጥብጦ እየጋተን
ጠላትና ወዳጅ ፣ መለየት አቃተን ።

ክብርና ውዳሴን ፣ ሳይሰስት ለሰጠ
ከወርቅ ሚዛን ላይ ፣ ወስዶ ባስቀመጠ
በሱሴ መደመር ፣ እየተሸጎጠ
ህዝብን ሲሸነግል ፣ መስሎት የበለጠ
ካናቱ ላይ ቆሞ ፣ ዛሬ እያላገጠ
ትዕቢት ከነፋው ፣ አለልክ ካበጠ
ወዶ አተላ ሲሆን ፣ ከታች ከዘቀጠ
በእስስት ባህሪው ፣ ከተለዋወጠ
የሰቀለ ያወርዳል ፣ እየዘረጠጠ ።

ጃዋርና ለማ ፣ ያሰማሩት ጀሌ
የደንቆሮ አበጋዝ ፣ የኦህዴድ ሎሌ
የጠገበው ወይፈን ፣ የላሰው አሞሌ
የመከራ አቀንቃኝ ፣ ጭጋግ እንደ ሃምሌ
የቦዘኔ መንጋ ፣ ሥራ ፈት ባተሌ
ኬኛ ኬኛ አበዛ ፣ ጨብጦ ብርሌ ።

ይዘው ያየናቸው ፣ ሜጫና ገጀራ
የፅንፈኛው ኦነግ ፣ ሰርገኛ ሙሽራ
የአብይና ለማ ፣ ያለበት አሻራ
የፅልመት አርበኛ ፣ ጥንስስ የመከራ
በየ አደባባዩ ፣ ወጥቶ የሚያቅራራ
የሚያደነቁረን ፣ ሲጮህ እንደ ቁራ
ድካም ከመሰለው ፣ ቄሮው የተፈራ
የቁርጥ ቀን ስትደርስ ፣ መች እንደ ፉከራ
ነገ እምናየው ነው ፣ ሱሪ ላይ ሲታራ ።

ታዛቢው

March 11, 2019